# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# ሁለተኛው ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

## የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ተግባቦት አገልግሎት ፓኬጅ

ሐምሌ 2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ

1. መግቢያ ........ 1
2. የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ተግባቦት ዓላማ ........ 2
2.1. አጠቃላይ ዓላማ ........ 2
2.2. ዝርዝር ዓላማ ........ 2
3. የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ተግባቦት መርሆች ........ 2
4. በኤክስቴንሽን ባለሞያዎች የሚከናዎኑ ዝርዝር ተግባራት ........ 3
ተግባር 1፡ዳሰሳ ማካሄድ ........ 3
ተግባር 2፡ ዕቅድ ማቀድ ........ 3
ተግባር 3፡ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማካሄድ ........ 3
ተግባር 3.1 የተናጠል ተግባቦት ማካሄድ፡- ........ 3
ተግባር 3.2 የቡድን ውይይቶችን መምራት ........ 6
ተግባር 3.3 የአድቮኬሲ ስራ መስራት ........ 8
ተግባር 3.4 የማህበረሰብ ንቅናቄ (Social mobilization) ........ 9
ተግባር 3.5 የማህበረሰብ ውይይት (Community Conversation) ........ 11
ተግባር 3.6 በድርድርና ተግባቦት ክህሎት ላይ ለ1ለ5 መሪዎች ስልጠና መስጠት ........ 13
ተግባር 3.7 የትምህርት ቤት ጤናን ማጠናከር ........ 13
ተግባር 3.8 የጤና ቀናትን ማክበር ........ 13
4. በጤና ኬላው ለጤና አጠባበቅና ተግባቦት ተግባር የሚያስፈለጉ ግብዓቶች፡ ........ 14
5. ከክላሰተር ጤና ጣቢያ ጋር መኖር ያለበት የስራ ግንኙነት ........ 14
6. የጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎት ክትትልና ግምገማ ማካሄድ ........ 14
7. ከጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎት የሚጠበቅ ውጤት ........ 15

## 1. መግቢያ

የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ለኅብረተሰብ ልማት ወሳኝና መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ጤና እና ልማት የተቆራኙና የማይነጣጠሉ ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም በጤናና ልማት ወደ ኋላ መቅረት ለበርካታ የጤና ችግሮች ይዳርጋል። በአብዛኛው ለችግሮቹ ዋነኛ መንስኤዎች በግለሰብና በኅብረተሰብ የአኗኗር ዘይቤና ባህርይ ምክንያት የሚከሰቱ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለሆነም የበሽታን መንስኤና ስርጭት ተገንዝቦ ጤናማ ጉልበትና በሽታን መከላከል አዋጭና ውጤታማ ጉዳይ ነው።

ኅብረተሰባችን የጤና ባለቤት እንዲሆንና የራሱን ጤና በራሱ ማምረት እንዲችል ማድረግ ያስፈልጋል። ቢሆንም ግን ለህብረተሰቡ የጤና ትምህርት ለመስጠት የሚያስችል የተግባቦት ክህሎት ውስንነት የተፈለገውን ያህል ውጤት እንዳይመጣ ዋነኛ ማነቆ ሆኖ ቆይቷል።ይህ የተግባቦት ክህሎት ሁሉንም የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ፓኬጆች ለህብረተሰቡ ለማስረፅና መሰረታዊ የባህርይ ለውጥ ለማምጣት የጤና አክስቴንሽን ባለሙያዎች እንዲጠቀሙበት ለማስቻል በደረጃ አራት ትኩረት እንዲሰጥበት ተደርጓል።

ግለሰብ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ በቤታቸው መተግበር ያለባቸውን ጠቃሚ የጤና ተግባራት ለመፈጸምና የጤና አገልግሎት ፍላጎታቸው ለማሳደግ ውጤታማ የተግባቦት ክህሎት በመጠቀም ህብረተሰቡን ማስተማር ብሎም ግንባር ቀደም የጤናው ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ያስፈልጋል።ይህንኑ ተግባር ዕውን ለማድረግ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ውጤታማ የመግባባት እና የተግባቦት ክህሎት ማለትም የማማከር፣የአመቻችነት፣የድርድር የማሳመንና ወደ ተግባር እንዲቀይሩ የማድረግ እንዲሁም የማቀድና የማሳተፍ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችላቸው እውቀት፣ አመለካከትና የክህሎት ሊኖራቸው ይገባል።በመሆኑም የማህበረሰቡን ጤናማ የባህይ ለውጥ ለማሻሻል በሚሰሩበት ጊዜ ለስራቸው አጋዥ ይሆን ዘንድ ታስቦ ይህ የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ተግባቦት ፓኬጅ ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በሚያገለግል መልኩ ተዘጋጅቷል።

## 2. የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ተግባቦት ዓላማ

### 2.1. አጠቃላይ ዓላማ

ግለሰብ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ የዕውቀት፣ የአመለካከትና የባህርይ ለውጥ በማምጣት የራሳቸውን ጤና እንዲያመርቱ ፣ እንዲጠብቁና እንዲሁም የጤናቸው ባለቤት እንዲሆኑ ማስቻል፡፡

### 2.2. ዝርዝር ዓላማ

- ❖ ግለሰብ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ በሽታዎች ምንነት ስርጭትና መከላከል ትክክለኛና ግልፅ መረጃ እንዲያገኙና ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ማስቻል፣
- ❖ ግለሰብ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ በጤናቸው ላይ በዕውቀት የተመሰረት አወንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸውና ተግባራዊ የሆነ እርምጃ እንዲወስዱ ማስቻል፣
- ❖ ግለሰብ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ ጤናን ለማጎልበት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ማጎልበት፣

## 3. የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ተግባቦት መርሆች

- ❖ የጤና አጠባበቅ ትምህርት የአንድ ጊዜ ስራ ብቻ ሳይሆን ተከታታይነት ያለው፣ በዕቅድ ላይ የተመሰረተና በተደራጀ መልኩ የሚከናወን ተግባር ነው፤
- ❖ የጤና አጠባበቅ ትምህርት በተወሰኑ ተደራሲያን ብቻ የሚወሰን ሳይሆን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማዳረስ ታቅዶ የሚተገበር መሆን አለበት፤
- ❖ የጤና አጠባበቅ ትምህርት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መተግበር አለበት፤
- ❖ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ከዕቅድ ጀምሮ ትግበራና ግምገማ ድረስ አሳታፊ መሆን አለበት፤
- ❖ ጤና አጠባበቅ ትምህርት በሳይንሳዊ እውነታዎችና መረጃዎች የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፤
- ❖ የጤና አጠባበቅ ትምህርት የማህበረሰቡን ባሕል ተጠቅሞ በአካባቢው የሚገኙ ግብዓቶችን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፤
- ❖ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መረጃ የሚሰጥ፣ የሚያዝና እና በሚስብ መልኩ መቅረብ አለበት ፡፡

## 4. በኤክስቴንሽን ባለሞያዎች የሚከናዎኑ ዝርዝር ተግባራት

የደረጃ አራት ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ማህበረሰቡን የባህርይ ለውጥ ለማምጣት የሚከተሉትን ተግባራት በአግባቡ መተግበር ይጠበቅባቸዋል፡-

### ተግባር 1፡ዳሰሳ ማካሄድ

በጤና አገልግሎት  አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ሀይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ለመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በሚከተለው መልኩ ዳሰሳ ማድረግ ፡-

- በዳሰሳው መካተት ያለባቸውን በየደረጃው ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍልና ባለድርሻ አካላት መለየት፤
- የዳሰሳ ጥናቱን ለማካሄድ የሚያግዝ መጠይቅ ማዘጋጀት (እንደመነሻ የሚያገለግል መጠይቁ በአባሪነት ተያይዟል)
- መጠይቁን በመጠቀም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ዋና ዋና የዕውቀት፣ የአመለካከት፣ የክህሎትና የተግባር ክፍተቶችን መለየት፣
- በዳሰሳው መሰረት ያገኝቸቸውን ውጤቶች ማደራጀት ማጠናከርና እንዲሁም ለቀጣይ ዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት መጠቀም፡፡

### ተግባር 2፡ ዕቅድ ማቀድ

ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን መረጃን መሰረት ያደረገና ግብን ያስቀመጠ የዕውቀት፣ የአመለካከት፣ የክህሎትና የባህሪይ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ስራዎችን ለመስራት  የሚጠቅም ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡

### ተግባር 3፡ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማካሄድ

የደረጃ አራት ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በተቀመጡት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ላይ የህብረተሰቡን ባህርይ ለመቀየር  የሚያስችሉ የድርድርና የተግባቦት ክህሎትና ስልቶችን በተሻለ ጥራት በመጠቀም የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ፡-

### ተግባር 3.1 የተናጠል ተግባቦት ማካሄድ፡-

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ቤት ለቤት በመሄድ በልማት ቡድንና በ1ለ5 ትስስር እየተሰራ ያለውን ስራ ለማጠናከር እንዲሁም ከአቅም በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ደግሞ በአካል ተገኝተው የባህርይ ለውጥ እንዲመጣ የተናጠል ድርድርና ተግባቦት ስራ ያስተምራሉ፡፡ በተጨማሪም ባለሙያዎች በ1ለ5 ያልተሳሰሩ አባ/እማዎራዎች ቤት ለቤት በመሄድ በተናጠል ያስተምራሉ፡፡ እንዲሁም ማህበረሰቡ በጤና ኬላ ለተለያዩ የጤና አገልግሎቶች  በሚመጡበት ጊዜ የተናጠል ተግባቦት የምክክርና የትምህርት አገልግሎት ይሰጣሉ፤

የትምህርትና የምክክር አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት፡-

- ጥሩ አድማጭ መሆን፣
- የመጠየቅና የማግባባት ችሎታ ፣
- የምክር አገልግሎት ተጠቃሚዋ/ው በሚገባው/ት ቋንቋ ማወያየት፣
- በውይይት ወቅት ወጥ የሆነና የተረጋጋ ባህርይ ማሳየት፣
- የምክር አገልግሎት ተጠቃሚዋ/ውን ችግርና ጭንቀት እንደራስ አድርጎ በመውሰድ መመካከር፣
- መሰረታዊ እውነታዎችን በማስረዳት ደንበኞች ተገቢ ውሳኔ እንዲወስኑ መርዳት፣
- ሚስጥርን መጠበቅ፣

በጤና ኬላ፣ ቤት ለቤት በሚደረግ የተናጠል ውይይት ወቅት የድርድር ክህሎት ደረጃዎችን በመጠቀም ማወያየት ያስፈልጋል፡፡

**የሚከተለው ሠንጠረዥ የድርድር ክህሎት ደረጃዎችን ከምሳሌ ጋር ያሳያል**

| **የድርድር ክህሎት ደረጃዎች** | በቀበሌው ልጆቿን ካለስከተበች እናት ጋር የሚደረግ ጉብኝት ላይ የድርድር ክህሎት ደረጃዎች አጠቃቀምን በተመለከተ የቀረበ ምሳሌ፤ |
|---|---|
| 1. ሰላምታ | ለእናትየዋ **ሰላምታ** ማቅረብና የጉብኝቱን ዓላማ መግለፅ |
| 2. መጠየቅ | ከአንድ ዓመት በታች ያሉ ሕፃናት ካሉና ክትባት ካልወሰዱ ለምን የሚለውን ጥያቄ **መጠየቅ** |
| 3. ማዳመጥ | የእናትየዋን መልስ በጥሞና **ማዳመጥ** |
| 4. ችግሩን መለየት | ልጆች ባለመከተባቸው ምክንያት የሚገጥመውን የጤና **ችግር መለየት**፤ |
| 5. መወያየት | ስለነዚህ የጤና ቸግሮች ከእናትየዋ ጋር በደንብ **መወያየትና** በሚወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች መተማመን፤ |
| 6. ምክራዊ አስተያየት | በቀጣይ ክትባት የሚሰጥበትን ቀንና ቦታ ማሳወቅና ልጆችን እንድታስከተብ **ምክራዊ ሃሳብ** መስጠት፤ |
| 7. መስማማት | እናትየዋ በቀረበው ሃሳብ **የምትስማማ** እንደሆነ ማየት የማትስማማ ከሆነ ለምን የሚለውን ጥያቄ በመጠየቅ ስጋቶች ካላት እንደገና በማብራራት ለመስማማት መሞከር፤ |
| 8. ቀጠሮ መያዝ | እናትየዋ በሚቀጥለው ለክትባት የምትመጣበትን ቀን **ቀጠሮ መያዝ** |

በጤና ኬላና ቤት ለቤት በሚደረግ የተናጠል ውይይት ወቅት ለውይይቱ ድጋፍ የሚሰጡ የመርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀም ደረጃ በመጠቀም ማወያየት ያስፈልጋል፡፡ ለሁሉም ፓኬጆች ማስፈጸሚያ እንዲውል የተዘጋጀውን የቤተሰብ መመሪያ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም ቤተሰብ ይህ መመሪያ እንዲደርሳቸው ማድረግ የግድ ነው፡፡

**የሚከተለው ሠንጠረዥ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያ አጠቃቀም ደረጃዎችን ከምሳሌ ጋር ያሳያል**

| | |
|---|---|
| የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያ አጠቃቀም ደረጃ | እንደ ምሳሌ የቤተሰብ ጤና መመርያን ተጠቅሞ የተናጠል ውይይት በሚካሄድበት ወቅት እንዴት መጠቀም እንዳለባት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡፡ |
| 1. ምልከታ | ተጠቃሚው/ዋ በምስሉ ላይ የሚታየውን **እንድትመለከት/እንዲመለከት** ማድረግ |
| 2. ማንፀባረቅ | ተጠቃሚው/ዋ የተመለከተችውን ነገር **እንድትገለፅ /እንዲገልፅ** ማድረግ |
| 3. ከራስ ጋር ማዋሀድ | በምስሉ ላይ የተመለከተችውን ተጨባጭ ሁኔታ **ከራሷ/ከራሱ ሁኔታ ጋር እንድታያይዝ/እንዲያይዝ** ማድረግ |
| 4. መተግበር | በምስሉ ላይ የተመለከተችውን/ውን **እንድትተገብር/እንዲተገብር** ማድረግ እንዲችል መርዳት፡፡ |

## ተግባር 3.2 የቡድን ውይይቶችን መምራት

### ሀ. የነፍሰ ጡር እናቶች ውይይት፡-

በቀበሌው ውስጥ ያሉ ነፍሰ ጡር እናቶች በእርግዝና ወቅት በቤታቸው መተግበር ያለባቸውን ተግባራት እንዲተገብሩ፤ በጤና ኬላው የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት እንደ ቅድመ ወሊድ፣ ወሊድና ድህረ ወሊድ የመሳሰሉትን አገልግሎቶች እንዲያውቁና ክትትል እንዲያደርጉ፤ ለወሊድ አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉና የመውለጃ ቦታ እንዲወስኑ እንዲሁም በእርግዝና ወቅትና በወሊድ ጊዜ የሚከሰቱ አደገኛ ምልክቶችን እንዲለዩና ምልክቶቹ ሲከሰቱም በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም እንዲመጡ ለማድረግ የምንጠቀምበት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ነው፡፡

የነፍሰ ጡር እናቶች ውይይትን ለመተግበር የሚከተሉትን ነገሮች ማከናወን ያስፈልጋል፡-

- ውይይቱን ከማካሄድ በፊት በቀበሌው የሚገኙ ነፍሰ ጡር እናቶችን ከ1ለ5ና የልማት ቡድን መሪዎች ጋር በትብብር መለየትና መመዝገብ፣
- ለውይይት አመቺና አማካይ የሆነ ቦታ ከተሳታፊዎች ጋር በመነጋገር መምረጥና መወሰን፣
- ለሚካሄደው ውይይት የሚሆነውን ርዕስ በመምረጥ አስፈላጊውን ዝግጅት ማደረግ፣
- በርዕሱ ዙሪያ ላይ ያለፈ ተሞክሮአቸውን የሚያካፍሉና አወንታዊ ተጽእኖ የሚያደርጉ አካላትን ለምሳሌ ሙሉ በሙሉ የቅድመ ወሊድ ክትትል ያደረጉና በጤና ተቋም የወለዱ

እናቶች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ባሎች፣ አማቶችና በጎ አመለካከት ያላቸው የልምድ አዋላጆችን ማሳተፍ ያስፈልጋል፡፡

**ለ. ከ2 ዓመት በታች ለሆኑ የህፃናት አመጋገብ ስርዓት ለማሻሻል የሚካሄድ ውይይት**

ከ2 ዓመት በታች ሕፃናት ያላቸው እናቶችን ለማወያየት የሚከተሉትን ነገሮች ማከናወን ያስፈልጋል፡-

- በቀበሌዋ ያሉ ህፃናትን መለየት፣
- ለውይይት ተስማሚ ቦታ መለየትና ማዘጋጀት፣
- ለውይይቱ ግብዓት እንዲሆን የህፃናትን ሁኔታ ለመረዳት እንዲረዳ የእድገት ክትትል ዳሰሳ በማድረግ መረጃ መሰብሰብ፣
- ለውይይቱ የሚረዱ ለምግብ ዝግጅት ሰርቶ ማሳያ አስፈላጊ ግብዓቶችን ማዘጋጀት፣
- ውይይቱን ማካሄድ፣ ሰርቶ ማሳያውን መተግበር እና እናቶች በየቤታቸው በተግባር ላይ እንዲያውሉ ስምምነት ላይ መድረስ፤

**ሐ. በቀበሌው የሚገኙ ከኤች. አይ. ቪ. ቫይረስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ጋር ውይይት ማድረግ**

- በቀበሌው ውስጥ ያሉ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩና በፈቃደኝነት ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንዳለ ለማህበረሰቡ ያሳወቁ ሰዎችን መለየት፣
- የህክምንና አገልግሎት መጀመርና አለመጀመራቸውን ማረጋገጥ፣
- በአቅራቢያቸው በሚገኝ የመወያያ ቦታ ተመርጦ ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ፣ የሚገጥማቸውን ችግሮች እንዴት መፍታት እንዳለባቸው እንዲሁም ተጓዳኝ የጤና ችግሮችን መካለከል የሚችሉባቸውን መንገዶች እንዲወያዩ ማመቻቸት፡፡
- ፈቃደኞች ከሆኑ ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ ለምሳሌ የሃይማኖት አባቶች ማህበራት እንዲገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**መ. ለክትባት አገልግሎት ከሚመጡ ተንካባካቢዎች ጋር የሚካሄድ የቡድን ውይይት**

- በክትባት የአገልግሎት ጣቢያ ለክትባት አገልግሎት የሚመጡ እናቶችን አገልግሎቱን ከማግኘታቸው በፊት የቡድን ምክክር አገልግሎት መስጠት ፣
- ለክትባት የሚመጡ እናቶች አጋጣሚውን ተጠቅሞ ሌሎች የጤና ጉዳዩችን በመለየት የውይይት አጀንዳ ማድረግ፣
- አገልግሎቱን ከመስጠት በፊት ለክትባት አገልግሎት የመጡ እናቶችን በቡድን በቡድን በማድረግ በጋራ ጉዳይ ላይ ለምሳሌ ክትባት ማስጨረስ፣ የቤተሰብ እቅድ መጠቀም፣ ጡት ማጥባትና ተጨማሪ ምግብ የመሳሰሉትን የቤተሰብ ጤና ካርድ በመጠቀም ምክር መስጠት ተሞክሯቸውንም እንዲለዋወጡ ማመቻቸት፣

- ❖ በቀጣይ ክትትል የሚያስፈልጋቸውን ለጤና ልማት ቡድን አባላት ማስተላለፍ፣
- ❖ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በውይይቱ ወቅት ሰርቶ ማሳያ መጠቀም፡፡

ለምሳሌ፡- የስነ ምግብ ችግር ላለባቸው በቤታቸው ከሚገኙ የምግብ አይነቶች እንዴት አድርግው የተደባለቀ ምግብ ማዘጋጀት እንደሚችሉ ሰርቶ ማሳየት

***የቡድን ውይይት የመምራት ሂደት፡-***

ከላይ ከሀ- መ የተዘረዘሩት የቡድን ውይይቶች በሚመቻቹበት ወቅት የሚከተሉትን ሂደቶች መከተል ፡-

- ❖ ስብሰባውን በምስጋናና በአክብሮት መጀመር፣
- ❖ የስብሰባውን ዓላማ መግለጽና ተሳታፊዎች እንዲተዋወቁ ማድረግ፣
- ❖ ለውይይት መነሻ የሚሆን የመወያያ ነጥቦችን መረጃን መሰረት አድርጎ ማቅረብ፣
- ❖ የውይይቱን መነሻ መሰረት አድርገው ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልጹ ማመቻቸት፣
- ❖ ሀሳባቸውን የገለፁትን ማመስገንና ሌሎች ያቀረቡትን ሃሳብ ማክበር ፣አለመንቀፍ እንዲሁም በርዕሱ ላይ ተሞክሮ ያላቸውን ሰዎች ተሞክሮአቸውን እንዲያካፍሉ መጋበዝ፣
- ❖ ከርዕሱ የሚወጡ ተሳታፊዎች ወደ ጭብጡ እንዲመለሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ❖ በተደጋጋሚ ዕድል የሚወስዱ ተናጋሪዎችን ሀሳባቸውን በማድነቅ ለሌሎች ዕድሉን ላላገኙ ተሳታፊዎች እድል መስጠት፣
- ❖ ተሳታፊዎች የተስማሙባቸውን የስምምነት ሀሳቦች በመለየት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያቅዱ ማድረግ
- ❖ የተስማሙባቸውን ተግባራት መከናወናቸውን ከ1ለ5ና ከልማት ቡድን መሪዎች ጋር በመሆን ተግባራዊነቱን መከታተል፡፡

## ተግባር 3.3 የአድቮኬሲ ስራ መስራት

- አድቮኬሲ በቀበሌ ደረጃ የውሳኔ ሰጪ አካላትን ይሁንታ እገዛና ድጋፍ ለማግኘት እንዲሁም ሀብትን ለማሰባሰብ የምንጠቀምበት ስልት ነው ፡፡
- በአድቮኬሲ የሚፈቱ ችግሮች በቤት ለቤት ድጋፍና በ1፡5 የልማት ቡድን መፈታት ያልቻሉ ነገር ግን የአመራሩን ተሳትፎ የሚሹ ጉዳዮች መሆን አለባቸው፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አድቮኬሲ ሲያካሂዱ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናዎን ይኖርባቸዋል:-

- ➢ በአድቮኬሲ የሚፈቱ ጉዳዮችን መለየት፣
- ➢ አድቮኬሲው የሚመለከታቸውን አካላትን የቀበሌ አመራር፣ የኅጥ መሪ፣ የሴቶች አመራር መለየትና የተግባር ዕቅድ ማውጣትና የአድቮኬሲ ክህሎቶችን ተጠቀሞ መተግበር፡፡(እገዛ የሚያስፈለግ ከሆነ እገዛ የሚያደርጉ አካላትን መጠየቅ)

**የአድቮኬሲ ስራ እንዴት እንደሚሰራ የሚያሳይ ምሳሌ፡-**

አበበች የግራር ቀበሌ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ነች፡፡ በቀበሌዋ የሚገኙ ነፍሰጡር እናቶች በሰለጠነ ባለሙያ በጤና ተቋም እንዲወልዱ ከልማት ቡድን መሪዎች ጋር በትብብር እየሰራችና መልካም ውጤት እያስመዘገበች ትገኛለች፡፡ ነገር ግን አሁንም በጤና ድርጅት የሚወለዱ እናቶች ቁጥር አናሳ ነው፡፡ ይህን ችግር ከልማት ቡድን መሪዎች ጋር ስትወያይ ወደ ተወሰኑ ጎጦች ከወረዳው የሚመጣ አንቡላንስ በድልድይ አለመኖሩ ምክንያት የማይገባ መሆኑን ተገነዘበች፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት የሚከተሉትን ተግባራት አከናወነች፡፡

1. መረጃ ማሰባሰብ፡- በጤና ተቋም መውለድ ሲገባቸው በቤታቸው የወለዱ እናቶች ከፍ ማለቱን ተገነዘበች፡፡ ከመገንዘቧም በላይ ከሌላ ቀበሌዎች ጋር ሲወዳደር ዝቅተኛነቱን በመረጃ አረጋገጠች፡፡
2. ከቀበሌ አስተዳዳሪ ጋር በመነጋገር የካቢኔ አባላት፣የሴቶች ማህበር አመራር፣ የወጣቶች ማህበር አመራር ማወያየት እንደምትፈልግ ዕቅዷን አቅርባ ከስምምነት ላይ ደረሱ፡፡
3. ለተሰብሳቢዎቹ ስለጉዳዩ ያጠናቀረችውን መረጃ እያነፃፀረች አቀረበች
4. በመጨረሻም ከተሰብሳቢዎቹ ጋር ችግሩ አንገብጋቢና መፍትሄ የሚያስፈልገው መሆኑን ስምምነት ላይ ደረሱ

**በአድቮኬሲው የተገኘ ውጤት፡-** በመጨረሻም የቀበሌው አመራርና የሚመለከታቸው አካላት በውይይቱ አምነው ከቀበሌውና ከማህበረሰብ በተገኘ የበጀትና የጉልበት ድጋፍ ድልድዩን በመስራታቸው ቤት የሚወለዱ እናቶች ወደ ጤና ተቋም በመሄድ መውለድ ጀምረዋል፡፡ አበበችም የመጣውን የተሻለ ውጤት ለቀበሌው አመራር አሳወቀች፡፡

***ማስታዎሻ፡-*** ከላይ በሳጥን ውስጥ በተጠቀሰው ማሳያ መሰረት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በስራ አካባቢ የሚያጋጥማትን ችግር ለመፍታት ውጤታማ የሆነ የአድቮኬሲ ስራ ማካሄድ አለባቸው፡፡

## ተግባር 3.4 የማህበረሰብ ንቅናቄ (Social mobilization)

- የማህበረሰብ ንቅናቄ ማለት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ማህበረሰቡ ዘላቂ በሆነ መልኩ በአጠቃላይ በጤናው እንቅስቃሴ ከእቅድ ጀምሮ ተሳታፊ እንዲሆን ማስተባበር የሚያስችል ስልት ነው፡፡
- በቀበሌ ደረጃ ሊኖሩ የሚችሉ ባለድርሻ አካላት የመንግስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች እንደ ትምህርትና ግብርና፣የህዝብ አደረጃጀቶችና ማህበራት እንደ ሴቶች ማህበርና ወጣቶች ማህበር፣ የሃይማኖት ተቋማት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በዚህም መሠረት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የማህበረሰብ ንቅናቄ በሚያካሂዱበት ወቅት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን፡-

- ❖ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ፓኬጆቹን መሰረት ያደረጉ የማህበረሰብ ንቅናቄ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚተገበሩ ዝርዝር የማህበረሰብ ንቅናቄ የሚያስፈልጋቸውን ተግባራት ትለያለች

እንደ ምሳሌ የሚከተለውን ሰንጠረዥ ምን አይነት ስራዎች ከእነማን ጋር መስራት እንደሚያስፈልግ ያሳያል

| **ተቋም/ማህበራት** | **በጋራ የሚሰሩ ስራዎች** |
|---|---|
| ወጣት ማህበር | ጠለፋና አስገድዶ መድፈርን ለመግታት፣ ያለድሜ ጋብቻን ለማስቀረት፣ አልኮልና አደንዛዥ ዕፅ ጉዳት ላይ ወ.ዘ.ተ |
| የሀይማኖት ተቋማት | እንደተወለዱ ክትባት ያለመጀመር ክርስትና ሳይነሳ በሚል፣ ጤና ተቋም አለመውለድ፣ ነፍሰ ጡር እናት አመጋገብ ከፆም ጋር በተያያዘ፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም በተመለከተ ወ.ዘ.ተ |
| የሴቶች ማህበር | በእርግዝና ወቅት የስራ ጫና ፣ ፆታዊ ጥቃት፣ በጤና አገልግሎት አጠቃቀም ላይ ውሳኔ አሰጣጥ ወ.ዘ.ተ |
| ዕድር | የነፍሰ ጡር እናት እንክብካቤ፣ ነፍሰ ጡር እናት በጤና ተቋም እንድትወለድ ማደረግ፣ ወላጅ አልባ ህፃናትን ማገዝ ወ.ዘ.ተ |
| ትምህርት ቤት | ወባ፣ ኤች.አይ.ቪ፣ የግልንና የአካባቢ ንፅህና፣ ያለድሜ ጋብቻ ወ.ዘ.ተ |

- ❖ ከላይ ከተዘረዘሩ ማህበራት /ተቋማት ጋር የጤና ችግሮች ላይ ውይይት በማድረግ እንደ ኃላፊነታቸውና የስራ ድርሻቸው ግብን መሰረት ያደረገ የጋራ ዕቅድ እንዲያወጡ ማድረግ፡፡

- ❖ የወጣውን ዕቅድ ተፈፃሚነት ክትትልና ሞያዊ ድጋፍ ማድረግ፡፡

- ❖ በወጣት ማህበር፣ በሴቶች ማህበር፣ በሃይማኖት አባቶች፣ በዕድሮች መካከል ከላይ በተለዩ የጤና ጉዳዮች ዙሪያ የወይይት መድረኮች እንዲዘጋጁ ማስተባበር፣ ውይይቱን መምራት፡፡

አስቴር በአሰፋቸው ቀበሌ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ ስትሆን በቀበሌዋ ውስጥ ከለየቻቸው የጤና ችግሮች ውስጥ ጠለፋና ያለድሜ ጋብቻ ፤ ከእምነት ጋር በተያያዘ ወደ ጤና ድርጅት ሂዶ አለመውለድ፤ የጤና አገልግሎት ከመጠቀም አንጻር የሴቶች ውሳኔ አናሳ መሆን እንዲሁም በኤች አይ.ቪ. ምክንያት ወላጆቻውን ያጡ ህጻናት መበራከት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በትብብር አብረዋት የሚሰሩ አጋር አካላትን ማሳተፍ እንዳለባት ተረዳች፡፡ ይህንንም ለመተገበር የሚከተሉትን ስራዎች መስራት ነበረባት ፡፡

1. በችግሮች ዙሪያ ላይ በቂ መረጃ መሰብሰብ ለምሳሌ በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ብዛትና ያሉበት ደረጃ፤
2. ለጤናው ስራ አጋዥ የሚሆኑ የሚከተሉትን አጋር ድርጅቶችን ለየች
   - የወጣት ማህበር፣
   - የሴቶች ማህበር
   - የሀይማኖት ተቋም
   - ዕድሮች ወ.ዘ.ተ
3. ከቀበሌው አመራር ጋር በመሆን ከአጋር አካላት ጋር ለመወያየት ቀጠሮ ያዘች
4. ለውይይት መነሻ የሚሆን ያዘጋጀችውን መረጃ ቀበሌውን ሊገልጽ በሚችል መልኩ አቀረበችላቸው፡፡ ችግሮችን ለመፍታት መደረግ ያለባቸው የመፍትሄ ሃሳቦች በተሳታፊዎች ከተሰነዘሩ በኋላ እያንዳንዱ አካል ምን መስራት እንዳለበት፣ መቼና እንዴት መፈፀም እንዳለበት ዕቅድ በማውጣት ተለያዩ


ለምሳሌ የወጣቶች ማህበር ከስብሰባው በኋላ ባለው አደረጃጀት የአልኮልና አደንዛዥ ዕፅ ለማስወገድ፤ያለእድሜ ጋብቻና ጠለፋ በማህበሩ ዘንድ የሚያስከተለውን ጉዳት ለመቀነስና ለማስወገድ ወጣቱን ለማወያየት በዕቅዳቸው ውስጥ አስገብተዋል

**ማስታዎሻ**፡- ከላይ በተጠቀሰው ማሳያ መሰረት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በስራ በአካባቢያቸው የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመፍታት ውጤታማ የሆነ የማህበረሰብ ንቅንቃቄ ስራ ማካሄድ አለባቸው፡፡

### ተግባር 3.5 የማህበረሰብ ውይይት (Community Conversation)

- የማህበረሰብ ውይይት ጠንካራና ጠቃሚ የመወያያ ዘዴ ሲሆን በህብረተሰቡ ውስጥ በጤናና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የባህርይ ወይም የድርጊት ለውጥ ለማምጣት የሚከናወን ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ አቀራረብ ነው፡፡ ይህ ስልት የሚያስፈለገው በህብረተሰቡ ውስጥ እየተተገበሩ ያሉ በጤናው ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ ማህበራዊና ጎጅ ልማዶችን በማህበረሰብ ደረጃ ለመቅረፍ ነው፡፡

የማህበረሰብ ውይይት ዋናዋና ደረጃዎች፡-




የማህበረሰብ ውይይት በሚካሄድበት ወቅት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማደረግ ይገባል፡

ሀ. ህብረተሰቡ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል አቅም እንዳለው መገንዘብ፤

ለ. ሁሉም ተሳታፊዎች በትጋት እንዲሳተፍ ማበረታታት ፤ ተወያዮች የሚያቀርቧቸውን ሃሳቦች ጠቃሚ መሆናቸውን መገንዘብ እንዲሁም ከርዕስ ሲወጡ የአመቻችነት ክህሎት ተጠቅሞ ወደ ርዕስ እንዲመለሱ ማድረግ ያስፈልጋል፤

ሐ. የህብረተሰቡ ወግና እሴቶችን ማክበር፤

መ. ከሌሎች አጋሮች ጋር ግንኙነት፣ ትብብር መፍጠር ( ከወጣቶች ማህበር፣ ከሴቶች ማህበር፣ ከዕድርና ወዘተ ጋር)፤

ሠ. እርስ በርስ ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልጹ ማድረግ፤

ረ. በወይይቱ መጨረሻ ላይ መተገበር ያለባቸውን ስራዎች ለይቶ በማውጣት ተፈፃሚነታቸውን መከታተል ያስፈልጋል፡፡

### ተግባር 3.6 በድርድርና ተግባቦት ክህሎት ላይ ለ1ለ5 መሪዎች ስልጠና መስጠት

- ❖ በተዘጋጀው ማሰልጠኛ ማኑዋል መሰረት የ1ለ5 መሪዎችን የአመቻችነት ክህሎትን በመጠቀም በድርድርና ተግባቦት ክህሎት ላይ ታሰለጥናለች፡፡ ለዚህ የሚያበቃት ግብዓት መኖሩን ታረጋግጣለት፡፡ (መመሪያዎች፣ የቤተሰብ ጤና ክብካቤ መመሪያ፣ የተለያዩ የጤና ትምህርት መርጃ መሳሪያች እንደአስፈላጊነቱ መጠቀም ትችላለች)
- ❖ የስልጠናውን ጥራት ትፈትሻለች፤ በስልጠናው የተገኙ ውጤቶችን ትገመግማለች፤

### ተግባር 3.7 የትምህርት ቤት ጤናን ማጠናከር

በቀበሌው ባሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎችን ሊያሳትፉ የሚችሉ የተለያዩ የጤና ክበባት ( የግልና የአካባቢ ንፅህና፣ የልጃገረዶች፣ ፀረ ኤ.ች.አይ.ቪ. ፣ ፀረ ወባ ወ.ዘ.ተ ክበብ) ታቋቁማለች፣ታጠናክራለች፡፡

- ❖ እነዚህን ክበባት በመጠቀም ወደ ማህበረሰቡ ሊወርዱ የሚችሉ ጤናን የተመለከቱ ድራማዎችና ስነ ፅሁፎች በማዘጋጀት በተለያዩ ስብሰባዎች (በሴቶች ማህበር ስብሰባ፣ በወጣቶች ማህበር ስብሰባ፣ የነፍሰ ጡር እናቶች ስብሰባ፣ በወርሃዊ የልማት ቡድን ስብሰባ ወዘተ) እንዲቀርብ በማድረግ የጤና ትምህርቱን ተደራሽነት የጎላ እንዲሆን ትሰራለች፡፡
- ❖ በትምህርት ቤቶች የተቋቋሙ ክበቦች መተግበር ያለባቸውን የጤና ፓኬጆችበመለየት ከተቋቋሙበት አላማ አንፃር እንዲታቀዱ በማድረግ ስራዎቹ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ታደርጋለች፤ አስፈላጊውን ክትትል ትሰጣለች፡፡

### ተግባር 3.8 የጤና ቀናትን ማክበር

በአገራችን የሚከበሩ የተለያዩ የጤና ቀን በዓላት አሉ፡፡ እነዚህን በዓላት ከሚመለከተቻው አካላት ጋር በመሆን ማክበር ያስፈልጋል፡፡ በዓላቱን ማክበር ኅብረተሰቡን በማነቃነቅ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለመፍጠር ብሎም የጤና አገልግሎት ፍላጎቱን ለማሳደግ እና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ይጠቅማል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ በዓላቱ ሲከበሩ የሚከተሉትን ተግባራት ታከናውናለች፡-

1. በዓላቱን ለማክበር ከቀበሌው ካቢኔ እንዲሁም ከጤና ጣቢያ ጋር የጋራ ዕቅድ ማውጣት፣
2. ከጤና ጣቢያ ባለሞያወች ጋር በጋራ በመሆን ለጥያቄና መልስ የሚሆን ጥያቄዎችን ማዘጋጀት፣
3. ከትምህርት ቤት ክለባት ጋር በመሆን ለበዓሉ የሚስማማ ድራማ ቀድሞ ማዘጋጀት፣
4. ከማህበረሰብና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የፓናል ውይይት ማካሄድ፤

## 4. በጤና ኬላው ለጤና አጠባበቅና ተግባቦት ተግባር የሚያስፈለጉ ግብዓቶች፡

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መመሪያ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ፓኬጆች፣
- የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣
- የቤተሰብ ጤና መምሪያ ካርድና
- ሌሎች ማጣቀሻዎችና መመሪያዎች፡፡

## 5. ከክላስተር ጤና ጣቢያ ጋር መኖር ያለበት የስራ ግንኙነት

- ከማህበረሰቡ ጋር በምታደርገው ውይይት በጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎቱ ላይ በማህበረሰቡ የተነሱ ክፍተቶችን በመለየት ከጤና ጣቢያው ባለሙያዎች ጋር በመወያየት የጥራት መሻሻያ እርምጃዎችን መውሰድ፣
- የጤና አጠባበቅ ትምህርትን በተመለከተ የሚሰሩ ስራዎች ከጤና ጣቢያ ጋር ማቀድ፣ መተግበር፣ መከታተልና መገምገም፣
- የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች መቅረባቸውንና ስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣
- የጤና ትምህርትና ተግባቦት በተመለከተ በጤና ጣቢያ ፣ በጤና ኬላ ወይም ልማት ቡድንና በተናጠል የሚተላለፉ መልዕክቶች ትክክለኛነታቸውንና ወጥነታቸውን ማረጋገጥ፣

## 6. የጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎት ክትትልና ግምገማ ማካሄድ

የጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎት ክትትልና ግምገማ በየጊዜው ማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎት አፈፃፀምን በየጊዜው በሚከተለው አካሄድ መከታተልና መገምገም ያስፈልጋል፡፡

- በቀበሌው የጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎት የክትትል ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በዋናነትም ከቀበሌ አስተዳደር ተወካዮች፣ ከክላስተር ጤና ጣቢያ ባለሙያዎች፣ ከሴቶች ልማት ቡድን አባላት እና ከሌሎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል ተወካዮች በጋራ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፣
- ተጨባጭና እውነታውን የሚያመላክቱ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ መተንተን፣ በአግባቡ ማደራጀትና መጠቀም፣
- የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና ግብዓቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን መከታተል፣

- የጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አስተያየት መጠየቅና የሚሰጡትን ግብረ መልስ ለስራ ማሻሻያ ለግብዓትነት መጠቀም፣
- የተጠናከረ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለግብዓት በሆነ መልኩ መጠቀም፣
- የአጋር ድርጅቶች በኩል ሊተገበሩ የታቀዱ የጤና ተግባቦት ስራዎችን በአካል በመገኘት መከታተል፣
- በትምህርት ቤት የክበባትን እንቅስቃሴ መከታተልና ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎችን መገምገም፣
- የጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎት አፈፃፀም ከዕቅድ አንፃር መፈተሽና አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣
- በግምገማው ወቅት ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መለየት፣ ለወደፊቱ ዘላቂና ቀጣይ ለማድረግ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በጋራ ማስቀመጥ

## 7. ከጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎት የሚጠበቅ ውጤት

- በጤና ጉዳይ የተሻለ እውቀት ያለው ፣ አዎንታዊ አመለካከትን ያዳበረ፣ ጤናን ለማበልፀግና በሽታን ለመከላከል ጠቃሚ የሆኑ ተግባራት መተግበር የሚችል ማህበረሰብ፣
- የጤና አገልግሎት ፍለጎቱ ያደገ ማህበረሰብ ፣
- በጤና ጉዳይ ባለቤትነትን ያዳበረ ማህበረሰብ ፣
- የራስን ጤና በራስ ማምረት የቻለ ማህበረሰብ ፣
- የጤና አገልግሎቱን በተገቢውና በተሻለ ሁኔታ የሚጠቀም ማህበረሰብ ፣ በአካባቢው የሚደረጉ የጤና ስራዎች ላይ የሚሳተፍ ግለሰብ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ፣
- በጤና አጠባበቅ ትምህርት ዋነኛ አጀንዳ አድርገው የሚንቀሳቀሱ አጋር አካላት (ማህበራት፣ ሴክተር መስሪያቤቶችና የሃይማኖት ተቋማት)፣
- በትምህርት ቤትና በማህበረሰብ ደረጃ ንቁ ተሳትፎ የሚደርጉ የት/ቤት ክበባት

*አባሪ 1፡*

በአካባቢው ያለውን ያታዊ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ተፅኖዎችን ለመለየት የተዘጋጀ መጠየቅ ከዚህ  በታች የተቀመጠው መጠይቅ ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በቀበሌአቸው ዝቅተኛ ሽፋን ባላቸው የጤና አገልግሎቶች ላይ በማተኮር የችግሩን መንስኤ ለመለየት ያግዛቸው ዘንድ ተዘጋጅቷል፡፡በምሳሌነት በጤና ተቋማት የሚለዱ እናቶች ሽፋን ዝቀተኛ በሆነበት ቀበሌ የችግሩን ምንጭ ለመለየት የተዘጋጀ መጠይቅ  ቀርቧል ስለሆነም በሁሉም የጤና ፕሮግራሞች ላይ መጠቀም ይቻላል፡፡

1. እናቶች ለምን በቤታቸው መውለድ ይመርጣሉ?

---------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------

2. በጤና ድርጅት እንዳይወልዱ የሚከለክሉአቸው ምን ምን ያታዊ ተፅዕኖ አለ?

----------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------

3. በጤና ድርጅት እንዳይወልዱ የሚከለክሉአቸው ምን ምን ሀይማኖታዊ አመለካከቶች አለ?

----------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

4. በጤና ድርጅት እንዳይወልዱ የሚከለክሉአቸው ምን ምን ማህበራዊና ልማዳዊ አመለካከቶች አለ?

----------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------

5. በጤና ተቋም ለመውለድ የባልና የአማት አመለካከት ምን ይመስላል?

---------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------